# በፋሽስትነታቸው የሚኮሩ አስገራሚ ትግሬዎች!


## ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian semay)

getachre@aol.com


March 05/2015

ረዢም ጽሑፍ እና ረዢም ትግል መወጣት የማይሆንላችሁ አጭር አስተንፋሾች ይህ ጽሑፍ የማትዘልቁት ከሆነ ከመጀመር ተቆጠቡ። ትግል እና ታሪክ ለቁንጣን የሚነበቡ እና የሚፈተሹት ሳይሆኑ ትዕግስትን ይጠይቃሉ።

በ23 ዓመት የትግሬዎች ሥርዓት ውስጥ በአገራችን ኢትዮጵያ በርካታ የፋሺዝም ተከታዮችና ቡድኖች ከተገመተው ቁጥር በላይ በገፍ ተፈልፍለዋል። አስገራሚው ደግሞ፤ ያለ ምንም መሸፋፈን ፋሺዝም "መመሪያው" ያደረገው ፋሺስቱ ወያኔ የድፍረቱ ጥልቀት ይገርማል። በዜና ማሰራጫ መስመሮቹ የሚጥላቸው የቆሻሻ ክምር ብዙ ስለሆነ ለእያንዳንዱ ቆሻሻቸው መልስ መስጠት ስልችት ስላለኝ መልስ ከመስጠት ተቆጥቤ ነበር። ነብሳቸው ይማረው መምህሬ እና የልብ ወዳጄ የነበሩት ሟቹ ዶ/ር አለሜ እሸቴ Origin of Tribalisation of Ethiopian Politics: From Fascism to Fascism በሚለው በዓይነቱ ልዩ የሆነ በበርካታ ምሁራን የተደነቀ ምሁራዊ የምርም ጽሁፋቸው ላይ "በኒቶ ሙሶሎኒ" ኢትዮጵያን በጎሳ ለመከፋፈል ዛሬ ወያኔዎች እየተከተሉት ያሉትን አስተዳደራዊ ካርታ እና የሙሶሎኒ "Legge Organica" (the Charter) (ብሔር፤ ብሔረሰብ እና ሕዝቦች) የቀየሰው የቋንቋ ከልል ሥርዓት አስከባሪዎች ሆነው ወያኔን በማገልገል ላይ ያሉ፤ "የወያኔ አበባ ተቀባዮችና" ተባባሪ "ጀሌዎች" **የሆኑ፤** ከአዲስ አበባ፤ከምሥራቅ፤ከደቡብ እና "አማራ ክልል" ብሎ ከከለላቸው ቦታዎች የለቃቀማቸው "አጋሰሶቹ" ትግራይ "ደደቢት" እና "ደጀና" በረሃ ድረስ በአይሮፕላን ተጉዘው፤ የፋሺስቱቹ ምሽጎችና "ፋሺዝም" የተመሰረቱበት በረሃ እያደነቁ፤ ቁና ቁና እያስተነፈሱ አፋቸውን ከፍተው ላሃጫቸውን እያዝረከረኩ ፤ አንዳንዱም የደጀና ጠመዝማዛ ዳገት ቁልቁለቱ መውጣት አቅቶት በወያኔ አስጐብኚዎች ቂጡ እንደ ሴት ተደግፎ፤ እየተገፋ፤ አንገቱ ላይ በጠመጠሙለት ምትሓታዊ የኤሲያ እስላሞች "ኩሹኽ" (ሽርጥ) ሕሊናው ተማርኮ፤ የ40 ዓመት የትግሬ ፋሺሰትና የባንዳዎች ታሪክ ሲያደንቅ አድምጠናል። በኛ በኩል ደግሞ እንዳይታዩ የደበቁዋቸው የንጹሃን መቃብሮችና የ40 አመት ጉዟቸው ምን ይመስል እንደነበር መንገር ተገቢ ምላሽ ነው እና እነሆ።

ወደ ርዕሴ ከመግባቴ በፊት፤ በነገራችን ላይ አስቴር ማሞ የተባለቺው ምስኪን ኦሮሞ (ኦሆዴድ) የተናገረቺውን አደመጣችሁልኝ? ከሷ ይልቅ ስለ እሷ እኔ ተሳቀቅኩኝ "ውይ! እንዴት ማፈሪያ ነች!"። "በመላ አገሪቱ ካሉ የታሪክ አሻራዎች ቀዳሚ ሥፍራ የያዘ ይህ የጎበኘው ሥፍራ ነው" ብላ ስትል "ጀሌነት" እና ሕሊና የሌላቸው "ባዶ ቅሎች" ከየት ቆፍረው እንደሚያገኟቸው ይገርመኛል።



አስቴር ማሞ ማለት የህችው እና ፤ ውይ! አንዴት አፈርኩላት!

ያ ማነው ደግሞ ስሙን አላውቀውም "ድንች ፊት" የሚመስለው ሱዳናዊው ዘፋኝ አብደከሪም አል ካብሊ የሚመስለው "አዲሱ ፕረዚዳንታቸው?" ድንጋይ ላይ ተቀምጦ የተናገረውን ያዙልኝ። እግዚሃር ይይላቸውና "ፕረዚዳንት" ሲሉት ሰምቼ ልስቅ ፍለጌ እግዜር አንዳይቆጣብኝ አፌን ዘጋሁ። ውይ! ኢትዮጵያ እንዴት የነዚህ መጫወቻ ሁና ትቅር!) "የወያኔዎቹ በቅሎ ብፃይ ሃይለማርያም ደሳለኝን" እማ ተውት "ዓለም እና አፍሪካን" የሚለውጥ አስተሳሰብ የተመሰረተበት ታሪካዊ ሥፍራ ብሎ "ጠንጋራ ህሊናው" ሲምታታበት ሰምቼው አገሬ አንዲህ የመሰሉ ባዶ ጭንቅላቶች እንዴት እንደፈለፈለቻቸው ለኔ ትልቅ ጥያቄ-ሆኖብኛል።



ብፃይ ደሳለኝ የወያኔዎችን ኩሹኽ እንደ በቅሎ ሉጓም አንገቱ ላይ ጠምጥመውለት የለመደበትን የሚያሽከሙትን የወያኔዎችን ሸክም ለመሸከም ጥርሱን እያጋጨ፤ ወገቡን አለጥልጦ ዝግጅነቱን ሲገልጽ ነው። ይኼኛው ከጐኑ የተቀመጠው "ብእዴን" ደግሞ "ቆብ" ሰጥተው "ኩሹኽ" እና "ጃኬት" የነፈጉት፤ የተቀመጠበትን የዘመዶቹን ተራራ ሲነጥቁት ዘመዶቹን ሲገደሉበት እና ሲሰድቡለት የሚደሰት በቁሙ የተገነዘ የአማራ ማፈሪያ ነው።

አውነት እላችኋለሁ፤ የጣሊያን ፋሺዝም ከታዬ በኋላ፤ ፋሺዝምን የሚያደንቁ ሰዎች በምድራችን ይታያሉ የሚል ግምት ከቶ ምንም እምነት አልነበረኝም። "ፋሺስዝም ምንድነው? በሚል ርዕስ እና የወያነ ትግራይ ፋሺስት ተግባሮች እና የተከተላቸው መመሪያዎቹ እና ሥራ ላይ ያዋላቸው መርሃ ግብሮቹ፤ እንዲሁም በደህንነት ሥራ ያሰማራቸው "የጎስታፖ/ኤስ ኤስ" ባህሪ የተላበሱ፤በግድያ የተሰማሩ፤ ከከተማ ሌቦች እና ዘራፊዎች ጋር በመመሳጠር የሌቦች ሰንሰለታዊ ህዋ/ዋሃዮ (ሴል) በመዘርጋት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሕዘብን ንብረት ሲዘርፉ ከነስማቸው የተመዘገቡ "የወያኔ ጎስታፖዎች':- የሕዝባችን ህይወት እንዴት እንዳወኩት "የስቶክሆልም ሲንድሮም በሽተኞች......." በሚል ርዕስ ውስጥ ከጀርመን እና ከሙሶሎኒ ፋሺስት ስርዓቶች የሚያመሳስሏቸው ባህሪያቶቻቸውን ገልጫለሁ።ዛሬ ስለ ፋሺዝም አልተነትንም።

የ40 አመት የፋሺዝም ስርዓት ሲያከብሩ “ጎስታፖወቹ” በሚዲያቸው ቀርበው ባንደበታቸው ሲናገሩ ያደመጥኩትን **በሃይለስላሴና በደርግ** ጊዜ አማራ ነግሶ የተቀሩትን “ጎሳዎች” የረገጠበት ሥርዓት ነበር ሲሉ የዋሹትን አድመጫለሁ። ወደ ዋናው ርዕሴ ለመግባት በዚህ ሃቅ ልጀምር፤

አሮሞዎች፤- 35 ከፍተኛ ጀኔራሎች እና ሲቪል ሚኒስትሮች ቡልቻ ደመቅሳን ጨምሮ ሥልጣን ላይ ነበሩ፤

ትግሬዎች፡-ከራስ መንገሻ ጀምሮ 18 ትግሬዎች ሥልጣን ላይ ነበሩ።

ጉራጉዎች፡- ከደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ፤ እና ከፍሌ እርገቱ ጀምሮ 18 ጉራጌዎች በሥልጣን ላይ ነበሩ፤

ሐረር፤ሲዳማ፤ጋሞጎፋ፤ሶማሊ.ወላይታ.... 17 ባለ ሥልጣኖች ነበሩ፤

የመረብ ምላሽ /ኤርትራኖች/፤ ተወላጆች፤ 25 ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ነበሩ፤

### በደርግ ጊዜ፤ ደግሞ

መንግሥቱ ሃይለማርያም እናት ወላይታ አባት አሮሞ ፤ ደበላ ዲንሳ እና ከዚያ ተከትሎ አሮሞ፤ ትግሬ፤ አማራ፤ ሶማሊ፤ ኤርትራ ....ወዘተ ወዘተ... ባለሥልጣኖች ነበሩ። ታዲያ ባንዳዎቹ አማራ እያሉ ሆን ብለው የአማራ ጥላቻቸውን ለማንጸባረቅ ያለፉትን ሥርዓቶች በአማራነት እየከሰሱ እስከዚህ ተጉዘዋል። ውሸታቸውንም ተቀባይ አግኝቶ እስከዛሬ ቆይቷል። ያ ግን ከእንግዲህ ወዲህ አይሰራም። የኔን መረጃ ለመመልከት “Who ruled Ethiopia? The myth of ‘Amhara domination’ by Markos Lema MD, PhD August 23, 2004 ተመልከቱ።

ከዚያም ወያኔን የሚቃወሙ ተቃዋሚዎች “ደርግ” እና “ነፍጠኞች” (አማራዎ ለማለት ነው) ፤ ናቸው እያለ ወያኔ እየዋሸ ሲያስቸግረን ታማኝ በየነ “በደርግ ጊዜ ደርግን ሲያገልግሉ የነበሩ በርካታ ከፍተኛ ባለስልጣኖች እና ወታደሮች በርካታ ቁጥር ያላቸው የደርግ ሹሞኞች የነበሩ፤ ዛሬ ደግሞ ወያኔን እያገለገሉት ያሉትን የደረግ ሹሞች የነበሩትን ስም ዝርዝራቸው “ሎስ አንጀለስ” ስብሰባ ላይ ያቀረበውን “ደርግ?! ደርግ ማነው?! እስኪ እንፈታተሽ” የሚል ድንቅ የመልስ ምት የሰጠውን አድምጡ (በዩቱቡ አድራሻ ተለጥፏል፤ አድራሻው ግን ትዝ አይለኝም) ይህንን ሁሉ ማሕደር ስትፈትሹ ወያኔ ምንኛ “የውሸት ጐተራ” መሆኑን ታገናዝባላችሁ።

በቅርቡ “ትግራይ ማስ ሚዲያ” ብለው ‘ዩ-ቱብ’ ላይ ባሰራጩት የ40 አመት ትግላቸው የሚገልጹ በስዕለ ደምጽ የተቀነባባሩ የታጋዮቻቸውን ቃለ መጠይቅ ያዘጋጁትን ሥራ አድምጬ ከመገረም አልፌ፤ አንዳንዶቹ በግል ስለማውቃቸው፤ “የውሸት ፈጠራቸው እና ያነጋገረቻው ትዕቢታዊ ውጥረት” ሳደምጥ ባንዳ እና ወረበላ ጠመንጃ ከያዘ ከመንፈሱ ጋር ጠብ ከመግጠም አልፎ ሰው እና ታሪክ ይታዘበኛል የሚል ይሉኝታ እንደማያውቅ የታዘብኩበት አጋጣሚ ነበር።

የዛሬ አያድርገው እና የጦቢያ መጽሔት አንዳንዱ ጸሐፊዎቻቸው ዛሬ ከግንቦት 7 መሪዎችና ጋዜጠኞች ተብየዎች (አንድ ድንቅ ፀሐፊ “ከራባት ያሰሩ የኢሳያስ ድመቶች” ይሏቸዋል) ጋር ሳይላላሱና አንደ ግመል ሽንት ወደ ኋሊት ከመመለሳቸው በፊት ተወዳጅ በነበረው መጽሔታቸው በጦቢያ አምድ ላይ የሚከተለው ብለው ነበር ፤

“ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተውልድ በደረግ መርማሪ ኮሚሲዮን፤ከትምህርት ቤት ጀምሮ ለዚች አገር መኖር፤ ለክብሯና ለነፃነት መታፈር ያበረከቱት አስተዋጽኦ በማስታወሻ መልክ ሲያቀርቡ በመረጃው የተረዳነው የኢትዮጵያን የ60 ኣመት ትግል ነበር። የአንድ ሰው ዜጋዊ፤ ትውልዳዊና አገራዊ አስተዋጽኦ ያን ያህል ግዙፍ ሲሆን፤ እያንዳንዳችን ነገው ትውልድ የሚጠይቀን ከባድ ጥያቄ ሊታወሰን ይገባል።...ይላል ጦቢያ

አዎን እነዚያ ትውልዶች ጣሊያኖች አገራችንን ወርረው የባሕር ወደባችንን ለመንጠቅ ባሰፈሰፉበት፤ሕዝባችን ለመከፋፈል ባቀዱበት የጨለማ ጊዜ፤ የሕዝብ ብቻ ሳይሆን እንደ ጠ/ሚኒስትር አክሊሉ ሃብተውልድ የመሳሰሉ (ሰንክሳር የሚባለው እሳቸው የጻፉትን ማሕደር ያንብቡ) ግለሰብ ትግልና አስተዋጽኦ፤ ከባንዳዎቹ እና ከፏሺቶቹ መሪ ለኤርትራ ልቡ ከደማው፤ ለኢትዮጵያ የባሕር ወደብ እንዳይኖራት የታገለ ካሃዲው ኤርትራዊው መለስ ዜናዊ ጋር ሲነጻጸሩ ታሪክ እውነትም ብዙ ቆሻሻ መሪዎችንም የምታስተናግድ መሆኗን በ23 አመት (40 አመት) አይተናል።

እውነትም የጦቢያ አምደኞች እንደዘገቡት ለዚች አገራችን ከተራሮችዋ እኩል ሰማይ ጠቀስ ትልቅነት ያላቸው ሥራዎችን ሠርተው ያለፉና ያረፉ እንደ አክሊሉ ያሉ፤ ዛሬ ደግሞ አንደ ፕሮፌር አስራት ያሉ ዜጎችን የነበሩት ያህል ከሥር ከሥሩ አገር የሚያፈርሱ ከትግሬ ማህፀን እናት ወጥተዋል። በትግራይ የኢትዮጵያ የታሪክ ማሕደር ውስጥ ይህ ልዩ አሳፋሪ የታሪክ ምዕራፍ ያደርገዋል።

በግሌ በትግሬነቴ ያፈርኩበት ወቅት ከተውንም ትዝ አይለኝም። ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሜን ባንዳዎች የኢትዮጵያን የባሕር ወደብ ለኢትዮጵያ እንዳይሰጥ ከጠላት ጋር ቆመው ተታኩሰው፤ "ተመድ ጽ/ቤት" ድረስ ሄደው እና ደብዳቤ አስገብተው ተሟግተው በፓርላማቸውም ጭምር ያለ ምንም የታሪክ ፍርሃት ለኤርትራኖች መቆማቸው ነግረው "የባሕር ወደቦቿን" ካሳገድዋት በኋላ፤ ትግሬነቴ እጅግ አውልቄ መጣል ብችል ኖሮ፤ በመረጥኩ ነበር።በኢትዮጵያ ትግሬዎችና- በወያኔ ትግሬዎች" መካከል የታየዉ ፍጥጫ፤ ወያነ ትግራይ "በኢትዮጵያ ሰንደቃላማ" ላይ የወያኔ ባንዴራ" የበላይነት ለመስጠት የተደረገዉ ትግል ስመለከት በጣም መራራ የታሪክ ወቅት ነው!

ሻዕቢያ እና ወያኔ እያደረጉት ያለውን በተለይ ባልተማሩ የትግሬ እና ኤርትራ (የመረብ ምላሽ) ሴት እህቶቻችን ላይ የሕሊና ጠለፋ እና ባንዴራቸውን አስለብሶ እስክስታ እያስጨፈሩ የሚያደርጉት የሕሊና አጠባ በጣም አሳዛኝ ነው። አንዳንዶቹም ፓል ቶክ በመክፈት የአማራን ሕዝብ እስከመዝለፍ የደረሱ አሉ። ለምሳሌ ባፍሪካ ቀንድ አካባቢ እየተዘዋወረች ከአንዳንድ "ኤን ጂ ኦ" ጋር የምትሰራ ኒውዮርክ አካባቢ የምትኖር ለምሳሌ ወ/ሮ ከበደች የተባለቺው ከዚህ በታች በፎቶግራፍ የምታይዋት በቅጽል ስሟ "ሕድያት ትግራይ" ፤ "ገዛ ተጋሩ"፤ "ለጀራ" እየተባለች የምትታወቀው ጸረ አማራዋ እና "እንደ ትግሬ ሱሪ ማንም አልተፈጠረም" የምትለዋ ትምክሕተኛዋ እና የአማራ ገበሬዎችን በፋሺስቶች መፈናቀል እና መገደል ድገፏን የሰጠችና የተሳለቀች … *(አረ ብዙ ነገር ስትል ተቀድታለች።.... የተናገርኩትን ቃሌን ከዋናው ንግግሬ እየቆራረጡ ተጠቅመውበታል ብላ "በፍርሃትና በውሸት" ብትክድም ሙሉዉን ቃሏ የያዙ ብዙ ዓይነት የትምክህት እና ዘረኛ ንግግሯ የተቀዳው በብዙ ሰዎች እጅ ይገኛል)* የራያ መኾኒ/ጨርጨር ተወላጅዋ የመሳሰሉ ከተማሩ ሴቶች አንደበት ስታደምጡ፤ ይህ ድርጅት በጎሳ አደራጅቶ በሕብረተሰባችን ላይ ምን ያህል የህሊና ቡርቦራ አካሂዶ አስተሳሰባቸውን አወላግዶ እንዴት እንዳበላሻቸው ስንታዘብ እጅግ ያስገርማልም፤ ያሰዝናልም።


የገዛ ተጋሩ ፓልቶክ ባለቤት ይህች ነች ወ/ሮ ከበደች (ለጅራ፤ገዛ ተጋሩ፤ሕድያት ትግራይ...) የምትባለው።





ይህ ከላይ የምታዩት የደላቸው የትግሬ ወይዛዝርቶች የትግራይ ፌስቲቫልን ለማክበር ከውጭ አገር ወደ ትግራይ ለሄዱ ለእነ ወ/ሮ ከበደች (ለጅራ) የመሳሰሉት አምና መቀሌ አይሮፕላን ማረፊያ ላይ አቀባበል ሲያደረጉላቸው የሚያሳይ ሲሆኑ፤ከሥር የሚታዩት ህጻናት ታቅፈው፤ተኮራምተው፤ አዝነው፤ አገራቸው ከድታቻቸው፤ “ውጡ!” እየተባሉ ከደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም “ሽፈራው ሽጉጤ” በሚበላው ፋሺሰት የወየኔ ጎስታፓ ከሚያስተዳድረው ‘ከሲዳማ’ የተባረሩ አማራዎች፤ ከነህጻናቶቻቸው በየበረሃው ተጥለው ሲንከራተቱ የሚያሳይ የፎቶ መረጃ ነው።

ይህ ሁሉ ፋሺስታዊ ጉድ ታቅፎ እያለ፤ ባንዳዎቹ ለበርካታ ወራት 40 አመታቸውን በድምቀት ለማክበር ያለቆፈሩት ድንጋይ ያላፈሰሱት ገንዘብና ያልነዙት ዓይን አውጣ ውሸት አልነበረም። ጣሊያን የነደፈውን፤በቋንቋ ከልሎ፤ የአማራን ሕዝብ የሚያስጠቃ ለመጨው የአማራ እና ኦሮሞ ትውልድ እሳት ለኩሶ ለማጨራረስ ኦሮሞ በሚኖሩባቸው አርሲ አካባቢ

“ኦኖሌ ሃውልት ገንብቶ” ለመጪው ትውልድ አማራን በኦሮሞ ሕዝብ ላመስጠላት የአማራ ህጻናትን በካራ እንዲታረዱ ለማድረግ (ካሁን በፊትም ተደርጓል) እያስተባበረ፤ የርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳ ሆን ብሎ በጥናት እሳት እየለኰሰ ያለውን የ23 ዓመት ፋሺዝም ሕዝባችን እንዲረዳው ማድረግ ሃላፊነት አለብን።

ፋሺስቶቹ ሥልጣን ከመያዛቸው በፊት ትግራይ ጫካ ውስጥም ብዙ አዛውንቶች (ገዛኢ ረዳ፤ አቶ ገብረሊባኖስ መዝገቦ....) እየገረፈ በእሳት ከእነ ነብሳቸው ያቃጠለ፤ እነ አታኽልቲ ሥዩምን የመሳሰሉ ትግሬዎችን በህይወታቸው እያሉ ጉድጓድ ውስጥ ከትቶ የቆላ በረሃ የመሬት ዱዱቃ (ትሎች) በጆሮዎቻው ውስጥ ተራብተው ተልተው ዓይኖቻቸውን አፍርጠው፤ ሰርስረው ወደ ውጭ እስኪወጡ ድረስ ያደረገው አሳፋሪ የደደቢት ወረበላው ቡድን፤ ያንን ተግባሩ ሽፍኖ፤ “ፋሺስትነታችንን እንኰራበታለን” ብለው ለዓለም ሲናገሩ ከመገረም በላይ የሰው ልጅ ሕሊና እስከ ምን አህል ድረስ መበላሸት እንደሚችል አስተማሪ የታረክ ጊዜ ነው።

ባንዳዎቹ፤ ኢትዮጵያ ትበጣበጥ አትበጣበጥ ጉዳያቸው አይደለም። የሚገርመው ግን ውጭ አገር የሚኖሩ  የትግሬ ምሁራን እንደ እነ ተኰላ ሐጎስ እና ገላውዴዎስ አርአያ የመሳሰሉ፤ በነዚህ ፋሺስቶች “ኢትዮጵያ የተቦረቦረች፤ የተሰነጣጠቀች፤አንድ ጎሳ ወደ ሌላው ጎሳ አካባቢ ሄዶ ቋንቋው ካልተናገረ መስራት መኖር የማይቻልበት፤ ጥላቻ የነገሰባት አገር ሆናለች ፤የጎሳ ግድያዎች የተፈጸመባት አገር ሆናለች የሚል የቪዲዮ ማስረጃ ለሕዝብ በመቅረቡ ምክንያት፤ “ፌይልድ ስቴት” (የወደቀች አገር) አይደለችም እያሉ “በቃላት ስንጠቃ” ሲጫወቱ አንብበናቸዋል። ሃቁ ግን የትግሬ ሊሂቃን ሲክቡት እና ሲያደንቁት የነበሩትን መለስ ዜናዊ የነገረን ግን የሚከተለው ነው። ከ BBC HardTalk ጋዜጠኛው  Stephen Sackur ጋር ያደረገው ቃለ መጠይቅ እንዲህ ይላል፦

“....you're also telling me that if things go wrong, as they might, you said, this country could slip into anarchy like Rwanda. You said that to me. Does that suggest you've established a level of stability and confidence in the future that can sustain this country?"

Meles - "We are not out of the woods yet..."

ብሎ እቅጩን 

የባንዳዎቹ መሪ የነበረው በግዜር ቁጣ የተቀዘፈው አሁንም ከጫካ ሕሊና አንዳልወጡ ግልጽ ያደረገው ጉዳይ ነው።

ከጫካ ሕሊና ያልወጣው ወያኔ በረሃ ውስጥ ሲርመሰመስ በነበረበት ጊዜ፤ ምን ዓይነት ፋሺስታዊ ተግባር ይፈጽም ነበር ብለን ለመመዝገብ ብንጀምር በሺዎቹ መጻሕፍት ተጠርዞ አያልቅም። በጨረፍታ ስንፈትሸው ግን ከናዚዎቹ ያልተናነሰ ወንጀል ሲፈጸም ነበር። ከማንም ጎሳ ጋር አልተደባለቅንም የሚሉ፤ ከምድር ዓለም ሰዎች የደም የአጥንት ፍንጣቂ ያልተደባለቁ፤ ከሰማየ ሰማያት የወረዱ "ባለ ቁምጣ ሱሬዎቹ" ልዩ ፍጡሮች የሆኑት "የወረቅ ፍልቃቂዎቹ"፣ ከዚያ አስከ'ዚህ ድረስ ያደረሰዉ መንገዳቸዉ በታሪክ ማሕደር ሲፈተሽ "የተጓዙት ጉዞ"-"የኢትዮጵያ ትግሬዎችን" በማግለል፤ ሰም በማጥፋት፤ ትግሬዎች አይደላችሁም በማለት፣ በመግደል፣በማሰቃየት፣በመሰወርና በመደብደብ፤ በኢሰብአዊ ጭካኔ የታጀበ በሰዉ ልጆች ህይወት ላይ ወንጀል የፈጸሙበት ፋሺስታዊ በወንጀል የታጀበ የጠረና የደም ጉዞ ሲጓዙ በቦታው የኖሩ የዓይን ምስክሮች የዘገቡትን አንፈትሻለን።

ኢትዮጵያንና ሰንደቃላማዋን ያከበሩና የድረጅት ባንዴራ አናመልክም ባሉት "በኢትዮጵያ ትግሬዎች" ላይ ባንዳዎቹ የወያኔ ትግሬዎች ያደረሱባቸዉ የግፍ ግፍ የኢድሕ/አዲዩ ታጋይ የነበረዉ የ "አሞራ" መጽሃፍ ደራሲ አቶ ግደይ ባሕሪሹም ሁኔታዉን ላላያችሁና ላልሰማችሁ አዳዲስ ባለጀሮዎች ብትኖሩ እንደሚከተለዉ ያቀርብላችኋል።ማን ይቅበር የነበረ፤ ማን ይናገር የነበረ፤ ርግጠኛ ምስክርነቱን ወዳጄ ግደይ ባሕሪሹም የወያኔ ፋሺስቶች ተግባር ላላያችሁና ላልሰማችሁ አዳዲስ ባለጀሮዎች ብትኖሩ እንደሚከተለዉ ያቀርብላችኋል።

\<<...የሻዕቢያ ቅጥረኛ ወያኔም ትግራይ ዉስጥ በገጠሩ ኢትዮጵያዊነቱን ያልካደና እምነታቸዉን ያላመነዉን ገበሬ የከተማ ወዝአደር፣ምሁር "ኮራኹር አምሓሩ" "ሸዋዊያን ተጋሩ" (የአማራ ቡቹሎች ፤ሸዋዉያን ትግሬዎች) እያለች፣ የኢድሕ ታጋይ ቤተሰብ ዘመድና አዝማድ የተባሉትን ሁሉ በጠቅላላ በሬ እና ላሙን፣በግና ፍየሉን፣ አህያና በቅሎዉን ዶሮና የጎተራ እህሉን፣ማርና ቅቤዉን እየወረሰች ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር አጥፍታዋለች... >> ካለ በኋላ፤

"ከመጀመሪያ እስካሁን በኢትዮጵያዊነት ላይ ያነጣጠረ ነዉ።..."ኢትዮጵያዊ ስያሜ"- የትግራይም ተወላጅ እንዳይጠራበት ለረዥም ዘመን ከነበራቸዉ የቂም ስሜት በመነሳት ... "ስለትግራይ ሕዝብ ወርቅነትና ስለ ትግራይ፤አሁንም አሁንም ስለ ትግራይ፤ትግራይ ..፣ ወዘተ ነበር ትምህርታቸው.."

" በትግሬና በአማራ መካከል የከረረ ጠብ ተፈጥሮ የትግራይ ህዝብ ከመሃል አገር የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እየተጋጨና እየተቧጨቀ እንዲኖር ግፋ በል እያሉ አልቆፈሩት ተንኮል አልነበረም..."

"ታሪክ ይውቀሳቸው እንጂ አገር አንደያዙ፤አዲሱ የትግራይ ክልል ብለው ደጋግመው በአወጡት የመልክዓ ምድር (ካርታ) ላይ ከአማራው ጋር ለማቀያየም፤ ወልቃይት እና ጠገዴን ተሻግሮ አዲስ ድምበር ከመጠየቅ ይልቅ፤ ትናንት ሰጃዝማች ገብረስላሴ በወጨፎ ጠመንጃ የሸጡትን የአውጋሮ የእኒ ሓጀር፤የጐሉጅ፤የተሰነይ እና የከሰላን በር የኤርትራ ክፍለሃገር ኩታ ገጠም ድንበር፤ለምን አላወሱትም ታዲያ? ለምስክር የአያቶቻቸው የገብረስላሴ ዓይነት "ወጨፎ" ጠመንጃ ይዘው ድርጅታቸውን መመስረታቸውን እናውቃለን፤ አላጣነውም፡ ወጨፎ ባለውለታችን ነው ተብሎ ይሆን?.." ካለ በኋላ ወዳጄ ግደይ ባሕሪሹም በአሞራ መጽሀፉ ላይ፤ አሰቃቂው የወያኔ ፋሺሰትነት አንዲህ ሲል ይገልጸዋል።

ጥርሱን አግጥጦ በፈገግታ ያልተቀበላቸውን ሁሉ እየተጠረጠሩ እንደ እነ አቶ ገዛኢ ረዳ በቁመና በህይወት በእሳት ለብልበው መጥበስ፤ሲሰለቻቸው ደግሞ ስቃዩን ያሻሻሉለት ይመስል በቁመናው በጠባብ ጉድጓድ ውስጥ አስረው ፤ ምስጥና ድዱቃ በልቶት ህይወቱ እንድታርፍ ማድረጋቸው ከጀርመን ናዚ የከፋ ጭካኔ ለማድረስ የተመራመሩበት ብልሃት ነበር። ለምሳሌ ሃበተ ገብረተንሳይ፤ ተኽላይ ገብረመስቀል፤ ወይዘሮ ወርቂ ምንጭራ ፤ ከተማ ሽራሮ ውስጥ የወረዳው ራፖል ጸሓፊ የነበረ የልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም በጐን የተወለደ (አባቴ አልነገሩኝም ስለዚህ አልቀበልህም ያሉት) ወንድም የሆነው አቶ አታክልቲ ሥዩም እና ሌሎች ይህ ፋሽስታዊ የግድያ ድርጊት በሚከተለው ዘግናኝ በሆነ የናዚ ፋሺስቶች ግፍ አገዳዳል ተፈጽሞባቸዋል። ይላል ግደይ ባሕሪሹም።

"ደደቢት ከወያኔ መሰረታዊ ሜዳ ላይ፣ ዜሮ ስድስት (ባዶ ሹድሽተ) ተብሎ የሚጠራ እስር ቤት፤ ለትግራይ ሕዝብ የናዚ ስርዓት የሚፈጽሙበት ነበር።ይህ ከአደጉ በኋላ (ምስገበሉ) የተመለሱበት ሜዳ ስለነበር፤ ለሞት ተፈርዶ ወደዚሁ ሜዳ የሚላክ እስረኛ፤ ስጋውን በፍጹም አሞራ አልበላውም።የእስር ቤቱ ጭካኔና ስርዓት አጽረጋ ከተባለው ስፍራ እንደጀመሩት ዓይነት ነበር።

የኢዲህ ደጋፊ ነህ፣ ልጅህ ወይም ወንድምህ የኢዲህ ታጋይ ነው፣ ተብሎ ይያዝና፤ ወደዚሁ ዜሮ ስድስት "ባዶ ሹዱሽተ" እስር ቤት ይወሰዳል፤ እንደደረሰም ስለ ንብረቱ ብዛትና መጠን የትስ እንዳለ ይጠየቃል።መጠይቁ እንደበቃ ለጥቂት ቀን ደህና ቀለብ እየተሰጠው በሁለት በሶስት ቀን ውስጥ ከሌላ ተመሳሳይ እስረኛ ጋር እየተረዳዳ፣ ቢያንስ ሁለት ሜትር ጥልቀት ያለው ጉድጓድ 4) እንዲቆፍር ይታዘዛል፤ የጉድጓዱ ስፋት ወይም ዓይነት የሰው መቃብር አይመስልም፤ እንደ ውሃ ጉድጓድ ጠበብ ብሎ እየተቆፈረ አፈሩ ዙሪያውን ይከመራል፤ እስረኛው የቁም መቃብሩነ ጭሮ እንዳበቃ ይወጣና በገመድ እጅና እግሩ ታስሮ፣ ዓለም በቃኝ ወደ ቆፈረው ጉድጓድ ይመልሱታል።ወያኔዎች እስረኛቸው ከመሞቱ በፊት ሲሰቃይ ማየት በጣም ያረካቸዋል።ቶሎ እንዳይሞት ትንሽ ቂጣና ጥቂት ውሃ በሜንጦ መሳይ በገመድ (በመገለል) ያቀብሉታል።ሽንትም ሆነ ዓይነ ምድር መፀዳጃው ከዚያችው ጉድጓድ ውስጥ ነው።

አንዴ ወደ ቆፈራት ጉድጓድ ከተጣለ በኋላ፤ በምንም ተአምር መልሶ መውጣት የለም።እስረኛው በዚያች ጠባብ ጉድጓድ ውስጥ እግሩን መዘርጋትና፤ በጎኑ መተኛት አይችልም።ተጨብጦ መቀመጡ ከደከመው፣ አቅሙ ከቻለ ማድረግ የሚችለው መቆም ብቻ ነው።ኩርኩም ብሎ ቀን በፀሐይ ሃሩር፣ ሌሊት በብርድ በጤዛ እየተሰቃየ፤ የተፈጠረባትን ቀንና አገር ዘር ሲረግም፤ ከመሞቱ በፊት ከመሬቱና ከሰውነቱ በሚፈጠሩት ትሎች (ድቁቋ)፤ ሰውነቱ እየተበላ፣ በሰው ላቦትና በመሬት ሙቀት የሚፈጠሩት ትሎችም፤ መርዘኞች ስላልሆኑ ቶሎ አይገድሉትም።ቆዳውን ሰርስረው፣ ስጋውን በልተው፣ አጥንቱን መፈርከስ ሲጀምሩ፣ እስረኛው በመጨረሻው በአፍና በአፍንጫው በዓይኖቹም ትሎችና ድዱቋዎች ይፍለቀለቁና፣ አሰቃቂ በሆነ መርገም ህይወቱ ከላፈች በኋላ፣ በዚህ የመርገም ትእይንት የማይሰቀቁ ወያኔዎች በጉድጓዱ ዙሪያ ያለውን አፈር መለስ አድርገው፣ እጅ እግሩን ታስሮ እንደ ተኮረኮመ እዚያው ቅብር ያድርጉታል።" የአሞራ-መጽሐፍ ደራሲ ግደይ ባሕሪሹም።

*"እንባ እንባ ይለኛል ይተናነቀኛል*
*ግን እንባ ከየት አባቱ!*
*ርቋል ከረጢቱ*
*ሳቅ ሳቅም ይለኛል*
*ስቆ ላይስቅ ጥርሴ*
*ስቃ እያለቀሰች*
*መከረኛ ነብሴ።"*

ብሎ ደራሲ በዓሉ ግርማ ኦሮማይ መጽሐፉ ውስጥ የገጠመው ግጥም የወያኔ ባንዳ ፋሺስቶች ያለ ምንም ተጠያቂነት በሕዝብ ሕይወትና በሃገር ላይ እንዴት እንደተጫወቱበት የ40 አመት ታሪካቸው ሲዘከሩ ይህንን አሰቃቂ ድርጊታቸው እንድንዘክር ያስታወሰናል።

አመሰግናለሁ ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian semay) getachre@aol.com